# ኩራተኛው

## ድመት



በአደፍርስ ሀብቴ

Niguss
Digital Library

# ኩራተኛው ድመት

ድርሰት ከሩዝ ሄርማን
ትርጉም በአደፍርስ ሀብቴ
አንደኛ እትም 1990
ሁለተኛ እትም 1992


ሜጋ አሳታሚ ድርጅት

በዱሮ ጊዜ በጣም ውብ የሆነና በኩራቱ የታወቀ አንድ ነጭ ድመት ነበር ከድመቶች ሁሉ በቁንጅና ለእኔ ሚስት ለመሆን የምትችል አንድም አትኖርም በማለት ሁሉንም ይንቃቸውና ያንቋሽሻቸው ነበር።




ስለዚህ ወደአንዲት ብልህ ቀበሮ ዘንድ በመሔድ በትሕትና ሰላምታ ካቀረበላት በኋላ፣

«ወይዘሮ ቀበሮ ምን እንደማደርግ ንገሪኝ። አንቺ ብልህና ዐዋቂ መሆንሽን ስለማውቅ፣ ምክርሽን ለመጠየቅ መጥቻለሁ። ለእኔ የምትስማማ ሚስት ለማግባት ፈልጌ ነበር ግን እንዲህ ያለችዋንም የማገኝ አይመስለኝም። እባክሽ ከሁሉም ቆንጆ የሆነችዋን ንገሪኝ በማለት ጥያቄውን ያቀርብላታል።



«ደህና» በማለት ወይዘሮ ቀበሮ ከመለሰችለት በኋላ፣ «ካየኋቸው ሁሉ ጨረቃ ሩቅና ውብ ነች። በጨለማ ስለምታበራ፣ በብርሃንዋ ለሁሉም ደስታን ትሰጣለች። አዎን፣ ጨረቃ ከሁሉም ቆንጆ መሆንዋን ዐውቃለሁ አለችው።

«ጥሩ! በማለት ውሮ ደስታውን ከገለጸ በኋላ ስለዚህ የጨረቃን ልጅ አገባለሁ የጨረቃ ልጅ በጣም ቆንጆ ከሆነች ከዚህ የተሻለ ምንም ማድረግ አልችልም። ግን ከጨረቃ የተሻለች ትኖር ይሆን?» በማለት ጥያቄውን አቀረበላት።



«አዎን» በማለት ወይዘሮ ቀበሮ መለሰችለት። «ፀሐይ ከጨረቃ ትበልጣለች። በሰማይ ላይ በምታበራበት ጊዜ በጣም ሞቃትና በጣም ቆንጆ ነች። በጉልህ ብርሃንዋ ከቆንጆዋ ጨረቃ እንኳ ትበልጣለች» አለችው።

«በጣም ጥሩ» ሲል ውሮ ከመለሰላት በኋላ «ስለዚህ የፀሐይን ልጅ ማግባት አለብኝ። ፀሐይ በሰማይ ላይ ይህን ያህል ጉልህ ብርሃን የምትሰጥ ናት በጣም ብሩህ ሆና ታንጸባርቃለች። ከፀሐይ የተሻለች መምረጥ እንደማልችል ርግጠኛ ነኝ። ግን ከፀሐይ የበለጠች ትኖር ይሆን?» በማለት ጥያቄውን አቀረበላት።



«አዎን! አዎን!» በማለት ወይዘሮቀበሮ ከመለሰችለት በኋላ ደመና ከፀሐይ የጠነከረ ነው። ደመና በጣም የወፈረ ስለሆነ ፀሐይ እንኳን በውስጡ አልፋ ማንጸባረቅ ምንም አይቻላትም» አለችው።

«በዚህ ሁኔታ» አለ ውሮ፣ «ደመና ከፀሐይ ከጠነከረ የደመናን ልጅ ማግባት አለብኝ» አላት። ቀጥሎም «ግን ከደመና የጠነከረ ካለ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?» በማለት ጥያቄውን አቀረበላት።



«አዎን አለ ነፋስን እንደምታውቀው እርግጠኛ ነኝ። ነፋስ ከደመና የጠነከረ ነው። ሀገር ሁሉ በደመና ሊሸፈን ይችላል። ግን ነፋስ መንፈስ

እንደጀመረ ምንም ሳይቀር ደመናውን ሁሉ ጠራርጎ በአንድ ጊዜ ይወስደዋል» ስትል ወይዘሮ ቀበሮ መለሰችለት።

«ጥሩ!» ካለ በኋላ ውሮ፣ «ሐሳቤን ቀይሬአለሁ የነፋስን ልጅ አገባለሁ!» ብሎ ተናገረ።

«ነፋስ ይህን ያህል ኃይለኛ ከሆነ ሌላ የተሻለ ይኖራል ብዬ አላስብም» ካለ በኋላ፣ ትንሽ ቆይቶ የተለመደ ጥያቄውን፣ «ከነፋስ የበለጠ ይኖር ይሆን?» ሲል አቀረበላት።



«አዎን አለ» ስትል ወይዘሮ ቀበሮ ከመለስችለት በኋላ፣ «ያ ትልቅ ዛፍ ይታይሃል?» ብላ ጠየቀችው።

«አንዳንድ ጊዜ ነፋስ ሊያስጐነብሰው ይሞክራል። ግን ነፋስ ምንም በኃይል ቢነፍስ ዛፍ በጣም ጠንካራ ስለሆነ፣ ቀጥ ብሎ እንደቆመ ነው» አለችው።

«በእኔ ግምት» ካለ በኋላ ውሮ፣ ጠንካራው ነፋስ በዛፉ ዙርያ ቀንና ሌሊት እያጓራ ዛፉን መጣል ካቃተው የዛፍን ልጅ አገባለሁ። ግን ከዛፍ የጠነከረ ይገኝ ይሆን ወይዘሮ ቀበሮ?» ሲል ጥያቄውን አቀረበላት



«አዎን በርግጥ!» በማለት ወይዘሮ ቀበሮ፣ «እሳት ኣለ። እሳት ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ፣ ዛፍን ሊያቃጥልና ማንኛውንም የሚጠጋውን ሊያወድም ይችላል» አለችው።

«ጥሩ! ጥሩ!» ካለ በኋላ ድመቱ፣ እሳት በጣም ጠንካራና ኃይለኛ ከሆነ የእሳትን ልጅ አገባለሁ» ሲል ተናገረ በኋላ ትንሽ ቆየት ብሎ፣ ከእሳት የጠነከረና የተሻለ ይኖር ይሆን?» ሲል ጥያቄውን አቀረበ።



«ለምን አይኖርም?» ስትል ወይዘሮ ቀበሮ መለሰችለት እንዲህ ስትልም ነገረችው፣

«ዝናብ ከእሣት በጣም የጠነከረ ነው። ዝናብ በእሣት ላይ መውረድ እንደጀመረ ወዲያውኑ እሣቱ ይጠፋል የዝናቡ ውሀ በእሣት ለወደሙት ተክሎች እንደገና ህይወት ይሠጣቸዋል» ስትል መለሰችለት

በጣም ጥሩ! የዝናብ ልጅ ለእኔ ሚስት መሆን የምትችል ይመስለኛል። ግን ከዝናብ የበለጠ ኃይለኛ ይኖር ይሆን?» ሲል ውሮ የተለመደ ጥያቄውን አቀረበ።



«አዎ አለ» ስትል ወይዘሮ ቀበሮ መለሰችለት። «አንድ አሮጌ ቤት ዐውቃለሁ። ዝናቡ በላዩ ላይ ይወርድበታል ግን የቤቱ ግድግዳዎች ቀጥ ብለው እንደቆሙ ናቸው። ከነፋስም ሆነ ከዝናብ ቤቱን ይጠብቁታል ምንም አዲስ ተክሎች በውስ ሊበቅሉበት አይችሉም» አለችው።




«ቤትን መጉዳትና ማፍረስ የሚችል ማን እንደሆነም ዐውቃለሁ ከቤት ሥር የሚኖሩ አይጦች የቤትን መሠረት በመቦርቦር ጥንካሬውን ሊያዳክሙና ቀጥ ብሎ የቆመንም ግድግዳ ሊያፈርሱ ይችላሉ» አለችው።

«አሃ! እንዴት ደስ አለኝ!» ብሎ ውሮ ከጮኸ በኋላ፣ የአንቺን ሐሳብ ለመጠየቅ መቻሌ ዕድለኛ ብሆን ነው! የአይጥን ልጅ ላገባ መሔዴ ነው ሲል ተነሣ ማንም እንደእኔ አልታደለም! ግን መጀመሪያ አይጥን የሚያሠጋና የሚበልጣት ይኖር ይሆን? ከአይጥ የጠነከረ ምን ይኖራል?» ሲል ጥያቄውን አቀረበላት።




«በርግጥ ይኖራል» ካለች በኋላ ወይዘሮ ቀበሮ፣ «ተመልከት ውሪት እየመጣች ነው። ርግጠኛ ነኝ፣ ውሪትን ታውቃታለህ። ከአይጥ የበለጠ ጠንካራ ነች። ገና ብቅ ማለቷን ሲያዩ፣ አይጦች ሁሉ በፍርሃትና በሽብር ከመራወጣቸውም በላይ፣ ውሪት የያዘችው አይጥ ወዲያውኑ ለሞት ይበቃል። ውሪት ልክ እንዳንተው ብልህና መሰልህ ነች። እስከ ዛሬ ድረስ ውሮ ራስህን ከሌሎች ድመቶች ሁሉ የበለጥኩ ነኝ ብለህ በማሰብ ስሕተትን ስትፈጽም ቆይተሃል። ምን ዐይነት ሐሳብ የለሽነት ነው! ውሪት ልክ እንደአንተ ቆንጆ ናት በትክክል ለአንተ የምትሆን ጥሩ ሚስት እሷ ናት» በማለት አስረዳቸው።



ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ውሮ ምን ያህል ሞኝ እንደነበር ተገንዝቦ ወደቤቱ ተጓዘ። ከጉራውና ከትዕቢቱም ተላቀቀ። ውሮና ውሪትም ተጋብተው ከበፊቱ የበለጠ አስደሳች ኑሮ ጀመሩ።





NIGUSS
DIGITAL LIBRARY